Name
Address Line 1
Address Line 2
Address Line 3
Address Line 4
Address Line 5

Person ID: xxxxxx Application ID: IPPA xxxxxx

**የአለም አቀፍ ጥበቃ ህግ 2015 ለመጀመር የተደረጉ የሽግግር ዝግጅቶች**

Dear XXXXX,

በአሁኑ ጊዜ በስቴቱ ውስጥ የስደተኛ/ የንኡስ ጥበቃ እንዲሰጥዎት ያቀረቡትን ማመልከቻ በመጥቀስ ነው፡፡

ለአለም አቀፍ ጥበቃ (የስደተኛ ሁኔታ እና የንኡስ ጥበቃ) እና በስቴቱ ውስጥ የመቆየት ፈቃድ ማመልከቻዎችን መርምሮ ውሳኔ ለመስጠት በአለም አቀፍ ጥበቃ ህግ 2015 (የ2015 ህግ) **በዲሴምበር 31/2016** በፍትህና እኩልነት ሚኒስቴር የተጀመረው (‹‹የተጀመረበት ቀን››) ውስጥ የተደረጉ አዳዲስ ሁኔታዎችን ላሳውቅዎ እወዳለሁ፡፡

በ2015 ህግ ውስጥ አንድ ደንብ ተካቷል፡፡ በዚህ ደንብ ስር አንድ አመልካች ለስደተኛ ሁኔታና ለንኡስ ጥበቃ፣ ለአለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ለአየርላንድ ዜግነት መስጠትና ፍልሰት አገልግሎት ያመለክታል፡፡ የአለም አቀፍ ጥበቃ ጽ/ቤት (“IPO”) የተሻለውን የስደተኞች ማመልከቻ ኮሚሽነር ጽ/ቤት (ORAC) ን ይተካል፡፡ በ2015 ህግ መሰረት አዲስ የአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ ሲቀርብ IPO ወዲያውኑ አመልካቹ የስደተኛ ሁኔታ ወይም የንኡስ ጥበቃ ሊሰጠው እንደሚገባ ወይም እንደማይገባ ይመረምራል፡፡ ከእነዚህ ጋር በተያያዘ አሉታዊ የውሳኔ ሀሳብ ከተሰጠ ሚኒስቴሩ ያለምንም ተጨማሪ የደንብ ቀደም ተከተሎች ወይም የደብዳቤ ልውውጥ አመልካቹ በሀገሪቱ ውስጥ በሌላ ማንኛውም ምክንያት ( ሰብአዊ ወይም የግል ሁኔታዎችን ጨምሮ) እንዲቆይ ፈቃድ ሊሰጠው እንደሚገባ ወይም እንደማይገባ ውሳኔ ይሰጣል፡፡ ከዚህ

ሂደት ውስጥ የማይካተተው ማመልከቻው በ EU ደብሊን መመሪያ ማለትም ሌሎች አመራጭ ድርድሮች ተፈጻሚ የሚሆንበትን- ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚገኘውን የአለም አቀፍ ጥበቃ አመልካቾች ጥበቃ ቡክሌት (IPO 1) ክፍል 10 ይመልከቱ፡፡ - መሰረት መታየት እንዳለበትና እንደሌለበት እና ይህ ቀድሞ የነበሩ ደንቦች ማለትም ሚኒስቴሩ የስደተኛ ሙብት ከከለከለ ሚኒስቴሩም አመልካቹ ለድጎማ ጥበቃ ዕድል እንዲሰጠውና የሚያደርግና ወደ ሀገሩ እንዲመለስ ትዕዛዝ ለምን እንዳልተሰጠ ምክንያቱን የሚያስረዳበት የነበረው ላይ የተደረገ ለውጥ ነው፡፡

## ማመልከቻዎ ያለበት ደረጃ

የ2015 ህግ፣ ህጉ ስራ ላይ ከመዋሉ በፊት ለ ORAC የቀረቡ የስደተኛ ሁኔታና የንኡስ ጥበቃ ማመልከቻዎችን የሚመለከቱ ጊዜያዊ አንቀጾችን የያዘ ነው፡፡ በ2015 ህግ ስር እነዚህ ማመልከቻዎች በዚያ ህግ ስር እንዲታዩ ለአለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ይተላለፋሉ፡፡

የእርስዎ የአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ ከዚህ ጋር ተያይዞ ባለው የመረጃ ሰነድ (IPO 12) ክፍል 4 **ምድብ 2 (የስደተኛ ይግባኝ)** መሰረት የሚታይ ሲሆን የስደተኛ ሁኔታ ማመልከቻው ከ RAT በፊት ከመጀመሪያው ቀን በፊት ይግባኝ ተጠይቆበት ነገር ግን በ RAT በዚያን ቀን ውሳኔ ካልተሰጠበት በአለም አቀፍ ጥበቃ ህግ 2015 ስር የሚታይ ይሆናል፡፡ ፋይሎት ለንኡስ ጥበቃ ታሳቢ እንዲሆን ለ IPO ይላካል፡፡ በ ORAC (በRAT የሚወሰነውም ተፈጻሚ ይሆናል) ምክረ ሀሳብ የሚቀርብበት ማመልከቻ እንዲቆይ ይደረጋል፡፡ IPO ለንኡስ ጥበቃ ፈቃድ ካልሰጠ፣ ሚኒስቴሩ በስቴቱ እንዲቆዩ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ይግባኞት ለስደተኛ ሁኔታ ተቀባይነት ካላገኘ (ከተደረገ) እና ንኡስ ጥበቃ በ IPAT ከተደረገ ሁለቱ ይግባኞች የሚታዩት እንደ አንድ ሆነው የሚሰሙትም በአንድ ላይ ነው፡፡

**አሁን ያለው የስደተኛ ሁኔታ እና /ወይም የንኡስ ጥበቃ በህግ 2015 ወስጥ ባሉት የሽግግር አንቀጾች ስር የሚታይ እንደመሆኑ መጠን ሌላ የአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ ማቅረብ አይስፈልግዎትም፡፡ ሆኖም ግን ከዚህ ጋር የተያያዘውን የአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ መጠይቅ (IPO 2) ውስጥ አግባብነት ያላቸውን ቦታዎች በመሙላት የአለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ተጨማሪ መረጃ መቅረብ ይኖርብዎታል፡፡**

## የመረጃ ማስታወቂያና ሌሎች አባሪ ሰነዶች

የ2015 አዋጅ የሽግግር አንቀጾች ተፈጻሚነት የተወሰኑ ተጨማሪ ዝርዝር አፈጻጸሞች ‹‹**የመረጃ ማስታወቂያ- የሽግግር ዝግጅቶች (IPO 12)**›› በሚል ሰነድ ስር ተካተዋል፡፡ ይህ ደብዳቤ ከመረጃ ማስታወቂያው ጋር በማገናዘብ መነበብ ይኖርበታል፡፡

የሚከተሉት ሰነዶች ተያይዘዋል፡-

- ***የመረጃ ማስታወቂያ - የሽግግር ዝግጅቶች (IPO 12)፡፡***
- ***የአለም አቀፍ ጥበቃ አመልካቾች መረጃ መጸሀፍ (IPO 1) እና***
- ***የአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ መጠይቅ (IPO 2)፡፡***

**በእርስዎ መሞላት ያለበት የአለም አቀፍ ጥበቃ መጠይቅ ከፍሎች የትኞቹ ናቸው?**

የአለም አቀፍ ጥበቃ መጠይቅ (IPO 2) እንዴት መሙላት እንዳለብዎት የሚከተለውን መመሪያ ተሰጥቷል፡፡

**<u>ከስደተኛ ሁናቴ ጋር ከሚገናኘው በስተቀር (ጥያቄ 63 ሀ እና 63ለ) የአለም አቀፍ ጥበቃ መጠይቅ (IPO 2) ሁሉንም ክፍሎች መሙላት ይኖርብዎታል</u>**

IPO የአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻዎ እንዲከለከል የውሳኔ ሃሳብ ካቀረበ እርስዎ በሌላ ምክንያት በሀገርቱ ውስጥ ለመቆየት ፈቃድ ሊሰጠው እንደሚገባ ወይም እንደማይገባ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

ህግ 2015 ስራ ላይ ሲውል ደንቦቹ መቀየራቸውን ማወቅ ጠቃሚ ነው፡፡ <u>ሚኒስቴሩ ከዚህ በኋላ እርስዎ በሀገሪቱ ውስጥ ለመቆየት ለምን ሊፈቀድልዎ እንደሚገባ ምክንያቶችን እንዲያቀርቡ በመጋበዝ ደብዳቤ አይጽፍሎትም</u>፡፡ ይልቁንስ በዚያ ፋንታ IPO የአለም አቀፍ ማመልከቻ ጥበቃዎ እንዲከለከል የውሳኔ ሃሳብ ከሰጠ በሀገር ውስጥ የመቆየት ፈቃድ ያለመዘግየት ግምት ውስጥ የሚገባ ይሆናል፡፡

<u>ስለዚህ የአለም አቀፍ ጥበቃ መጠይቅ (IPO 2) አግባብነት ያላቸውን ክፍሎች ሲሞሉ ለምን ሀገር ውስጥ የመቆየት ፈቃድ ሊሰጥዎ እንደሚገባ በጽሁፍ ማንኛውንም ምክንያት ማስቀመጥ የእርስዎ ፋንታ ነው</u>፡፡ በምሳሌ መልክ የእርስዎ ቤተሰብና የቤት ውስጥ ሁኔታዎች፣ ከሀገሪቱ ጋር ያልዎት ቁርኝት አይነት በሀገሪቱ ውስጥም ሆነ ከሀገሪቱ ውጪ ያልዎት ባህሪእናነ ጸባይ እንዲሁም ግምት ውስጥ የሚገቡ ሰብአዊ ጉዳዮች በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሁሉም አስፈላጊ ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮች ናቸው፡፡ አስፈላጊ ስለሆኑ ጉዳዮች የተሟላ ማብራሪያ ለማግኘት የአለም አቀፍ ጥበቃ አመልካቾች መረጃ መጸሀፍ (IPO 1) ን ይመልከቱ፡፡

በሂደት የሚኖሩ ጠቃሚ ለውጦችን (ለምሳሌ፣ ቤተሰብዎት ወይም የአካባቢዎትን ሁኔታ ወይም የመጡበትን ሀገር ሁኔታ) ለ IPO (በሚኒስቴሩ ስም) ማሳወቅ ይኖርቦታል፡፡

**አሁን ምን  ማድረግ አለብኝ ?**
**የአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ መጠይቅ (IPO 2) አንዴ ሞልተዉ ሲጨርሱ እንዲታዩልዎ የሚፈልጉትን ከዚያ በፊት ለ ORAC ካላቀረቧቸዉ  ማንኛዉም ሌሎች ተጨማሪ መረጃዎች እና ሰነዶች ጋር በንጹህ ፖስታ አድርገዉ ለእኛ መመለስ አለብዎት፡፡ ይህ መጠይቁ ከተቻለ ይህ ደብዳቤ ከደሰዎ ቀን ጀምሮ በ20 የስራ ቀናት ዉስጥ ሊመለስልን ይገባል፡፡**

**ከላይ የተጠቀሰዉን መረጃ ካቀረቡ ቦኋላ እርስዎ እና /ወይም የህግ አማካሪዎ ሌላ ተጨማሪ መረጃ  ለ IPO ማቅረብ ከፈለጋችሁ  በተቻለ መጠን ወዲያዉኑ ማድረግ እና ይህንን ማድረግ የሚችሉ ከሆነ ለቃለ መጠይቅዎ ከተያዘልዎት ቀጠሮ ቀን ከሁለት ሳምንት ባልበለጠ ጊዜ ዉስጥ ማቅረብ ይኖርብዎታል፡፡ ይህም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሰነዶችን ለማስተርጎም ጊዜ የሚሰጥ እና  የ IPO ቃለ መጠይቅ አድራጊዉ  የእርስዎ ሁሉም ሰነዶች በእጁ መድረሳቸዉን እንዲያረጋግጥ እና ከቃለ መጠይቅዎ ቀን በፊት እንዲታዩ ለማድረግ ያስችላል፡፡**

**ቃለ-መጠይቅ**
ተሞልቶ የቀረበልንን መጠይቅዎን ከተቀበልን ቦኃላ IPO ለአለም አቀፍ ጥበቃ ቃለ መጠይቅ ቀን እርስዎን የሚያነጋግር ይሆናል፡፡ የእርስዎ ጉዳይ በEU ደብሊን መመሪያ መሰረት የሚታይ ካልሆነ በስተቀር ቃለ መጠይቅዎ የስደተኛ ሁኔታና የንኡስ ጥበቃ ጉዳዮችን ሁለቱንም የሚሸፍን ይሆናል፡፡ በ ORAC ለስደተኛ መብት  ቃለመጠይቅ የተደረገላቸው ነገር ግን ከሚጀመርበት ቀን በፊት የውሳኔ ሃሳብ ያልተቀበሉ አመልካቾች በድጋሚ በ IPO ቃለ መጠይቅ  ይደረጋሉ፡፡ IPO ብዙ ማመልከቻዎችን በማሰናዳቱ  ምክንያት ቃለመጠቅዎ ለብዙ ወራት ሳይቀጠር ሊቆይ ይችላል፡፡

**በሀገሪቱ ውስጥ ነዋሪነት**
በሀገሪቱ ውስጥ ያልዎት የነዋሪነት ሁኔታ ጋር የተያያዙ ነገሮች አይለወጡም፡፡ ቀደም ብሎ የተሰጥዎት ጊዜያዊ ምስክር ወረቀት (TRC) በ2015 ህግ ክፍል 17 ስር እንደተሰጠ ጊዜያዊ የመኖሪያ ምስክር ወረቀት ተደርጎ የሚወሰድ እና  ለአለም አቀፍ ጥበቃ ያቀረቡት ማመልከቻ ውሳኔ እስኪያገኝ ድረስ የሚያገለግልና ሊታደስ የሚችል ይሆናል፡፡

**የህግ ምክር**
ከዚህ ደብዳቤና አባሪ የተደረጉ ሰነዶች በተመለከተ የህግ ምክር እንዲያገኙ ይመከራሉ፡፡ የህግ አማካሪ የማነጋገር መብት ያልዎት ሲሆን ከህግ ድጋፍ ቦርድ አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ፡፡ የህግ ድጋፍ ቦርድ (LAB) በአየርላንድ ውስጥ  ለአለም አቀፍ ጥበቃ በማመልከት  ላይ ላሉ ሰዎች ሚስጥርነቱ የተጠበቀ የህግ አገልግሎት የሚሰጥ ገለልተኛ ኤጀንሲ ነው፡፡ LAB ማመልከቻውን በመደገፍ የህግ ድጋፍና እርዳታ ይሰጥዎታል፡፡ **የ LAB አድራሻ ዝርዝር አባሪ በተደረገው የመረጃ ማስታወቂያ( IPO 12)** ውስጥ ተካቷል፡፡

በራስዎት ወጪ የህግ ምክር ማግኘት ይችላሉ፡፡

የህግ ተወካይ ኖሮት እስካሁን ካላቀረቡ፣ ማቅረብ ይኖርቦታል እንዲሁም በህግ ተወካዮት ላይ ለውጥ ካለ ለአለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ በፍጥነት ያሳውቁ

**ዩኤንኤችሲአር (UNHCR)**

***የማግኛ ዝርዝሩ በመረጃ ማስታወሻው ላይ የተያያዘለት* (IPO 12)** የተባበሩት መንግታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር ማማከር ይችላሉ፡፡

***በፈቃደኝነት መመለስ***

የአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻዎትን መቀጠል ካልፈለጉ፣ ወደ መጡበት ሀገር በፈቃደኝነት መመለስ ይችላሉ፡፡

***የማግኛ ዝርዝሩ በመረጃ ማስታወሻው ላይ የተያያዘለት* (IPO 12)** ምክርና ድጋፍ ከአለም አቀፍ የስደተኞች ድርጅት (IOM) ማግኘት ይችላል፡፡

***አዲሱ የማመልከቻ ቁጥሮዎ***

የቀድሞ ማመልከቻ ቁጥሮዎ አያገለግልም፡፡ አዲሱን የማመልከቻ ቁጥሮትን ከ **IPPA** ደብዳቤ አናት ላይ ያገኙታል፡፡ የግል መለያዎት ተመሳሳይ እንደሆነ ይቀጥላል፡፡

***አድራሻዎት***

አድራሻዎትን ቀይረው ከለቀቁ በፍጥነት ለአለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ **በጽሁፍ** ያሳውቁ፡፡ እባክዎትን ደብዳቤው ላይ መፈረሞትንና **አዲስ** መጥቀሻ ቁጥር ማካተቶትን አይርሱ፡፡

***ጥያቄዎች***

በአለም አቀፍ ጥበቃ ወይም በዚህ ደብዳቤ ላይ ማንኛውም አይነት ጥያቄዎች ካሎት፣ ያግኙ (***አዲሱን መጥቀሻ ቁጥር* ያስገቡ**)፡-

**Customer Service Centre**
**International Protection Office**
**Irish Naturalisation and Immigration Service**
**79 - 83 Lower Mount Street**
**Dublin 2, D02 ND99**
**Telephone: 01 6028008**
**Email: info@ipo.gov.ie**

የዚህ ደብዳቤ ጽሁፍና እባሪዎች ለህግ አማካሪው ቅጂው ይደርሳል፡፡

**አለማቀፍ ጥበቃ ቢሮ**
**የአየርላንድ ዜግነት መስጠትና ፍልሰት አገልግሎት**
**Date**